**የወያኔ ክንፍ የሆነው ብአዴን አባላት በሕዝብ ቆጠራው ውጤት የተጠነሰሰው ቁጣቸው ስለ ጥቅማጥቅም በወጣው ረቂቅ ህግ የገነፈለባቸው መሆኑ ተዘገበ**

**በአማራው ላይ እየተለየ የተወሰደው እርምጃ ፖለቲካዊ ነው ማለታቸውም ታውቆዋል**

**የወያኔው የተወካዮች ምክር ቤት አባላት እርስ በእርስ ተጣሉ « በሰማእታት » ስም እየተለመኑ ስብሰባ ጥለው ወጡ**

**መለስ ዜናዊ ስልጣኔን እለቃለሁ በማለቱ በቡድን አባላቱ መካከል ፍትጊያ ተነሳ**

**ስልጣኔን እለቃለሁ የተለመደው የማደናገሪያ ስልቱ ነው ሲሉ ታዛቢዎች ተቹ**

**ስዩም መስፍን እጩ ይሁን በሚለው ሃሳብ በአርከበ እቁባይ ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠመው በመስከረም 2002 መጀመሪያ ላይ ይለይለታል**

**የረሃብተኛው ቁጥር 10 ሚሊዮን ደርሶ ወያኔ የእርዳታ እህል እንዳይገባ ከለከለ**

በወያኔው ቡድን ውስጥ የተጀመረው ትርምስ ውስጥ ውስጡን እየተፋፋመና እየጋመ መጥቶ በአደባባይ መሞሻለቅ መጀመራቸው ታወቀ

ባለፈው ሳምንት ውስጥ በተወካዮች ምክር ቤት የወያኔ አባላት ባነሱት ጥያቄ ላይ ሳይስማሙ በመቅረታቸው ለ17 አመታት ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ ስብሰባ ረግጠው እስከመውጣት መድረሳቸውን የደረሰን ዘገባ ገልጦዋል

በቅርቡ የባለስልጣናትን ጥቅማጥቅም የሚመለከት የህግ ረቂቅ ከወያኔ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ለወያኔው ፓርላማ የህግ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ እና ለማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የተመራ ከመሆኑም በላይ የወያኔ ሰዎች እንዲወያዩ ቢደረግም ያለስምምነት መጠናቀቁና ስብሰባውን ረግጦ እስከመውጣት ደርሰው በረቂቅ ህጉ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ማሰማታቸው ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልጦዋል

በህግ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የህወሃቱ አቀንቃኝ እና ካድሬ አስመላሽ እና በማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አዜብ መስፍን የሚመራ ስብሰባ በወያኔው ፓርላማ አዳራሽ ውስጥ የተደረገ ሲሆን በዚህ ስብሰባ ላይ የባለስልጣናትን ጥቅማጥቅም የሚየስጠብቅ ህግ ረቂቅ ዙሪያ ላይ መነጋገራቸውና የተሰናበተ ተመራጭ የ3 ወር ደሞዝ እንዲከፈለው ብቻ የሚፈቅድ ነው በሚለው ላይ አባላቱ ከፍተኛ ተቃውሞ ያሰሙ ሲሆን በተለይ የብአዴን ካድሬዎች የሆኑ የምክር ቤት አባላት « እስከ ዛሬ ድረስ በእኛ ትከሻ ስትጠቀሙ ቆይታችሁ ለራሳችሁ ሲሆን ዘላቂ ተጠቃሚ የሚያደርጋችሁን ህግ ስታወጡ እኛን ከህዝብ ጋር ስታጋጩ ኖራችሁ ። ዛሬ እጃችሁን አጣጥፋችሁ ተቀመጡ ሙልጫችሁን ቅሩ ማለታችሁ በእጅጉ የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ በእኛ ላይ ደባ እተፈጸመብን ነው » በማለት ሃይለ ቃል እንደተናገሩና የመሰብሰቢያአዳራሽ በቡድን ሆነው ጥለው መውጣታቸውን ዘገባው አስረድቶዋል

የእለቱ ስብሰባ መሪ የወያኔው መሪ የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን ከመቀመጫዋ ተነስታ እየለመነች ወደ አዳራሹ እንዲመለሱ ብትማጸንም « አንቺ በባልሽ በኩል አስፈላጊው ጥቅማጥቅም የተሙዋላልሽ እና ያስተካከልሽ ስለሆነ ሊሰማሽ አይችልም ፤ እኛ ግን ከህዝብ ጋር ተጣልተን ተጋጭተን ባለንበት በዚህ ወቅት ያለምንም አስተማማኝ ጥቅም ወደ መጣችሁበት ተመለሱ ማለት እራሳችሁን አጥፉ እንደማለት ይቆጠራል » እያሉ በዚያው ሳይመለሱ ወጥተው እንደሄዱ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተትችሎዋል

የህግ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አይነ ስውሩ የህወሃት ሰው አስመላሽ በበኩሉ « ይህ ዛሬ ተቀምጠን እየተነጋገርንበት ላለነው ቀን ያበቁን ሰማእታት በከፈሉት መስዋእትነት ነው ስለዚህ በሰማእታቶች ይሁንባችሁ ተመለሱና እንምከር » እያለ ቢወተውትም እያሽፉበትና እያላገጡበት በቡድን በቡድን በመሆን የስብሰባ አዳራሹን

ሁሉም ጥለው በመውጣታቸው ድንጋጤ ውስጥ የገቡት ሁለቱ የወያኔ ካድሬዎች ለበረከት ለመለስ ዜናዊ ወዲያውኑ ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን እነመለስም በዚያውኑ እለት ምሽት በሚኖሩበት ህንጻ ላይ ሁሉም ተሰብስበው ግምገማ እንዲደረግና ድርጊቱን የፈጸሙት የስም ዝርዝራቸው እንዲገለጽልን በማለት ትእዛዝ መስጠታቸውን ዘገባው ጨምሮ አስረድቲዋል

ምንም እንኩዋን መለስ ዜናዊና በረከት ስምኦን ድርጊቱን የፈጸሙትን የብአዴን ሰዎች ማንነት ለማጥራት ምሽት ላይ ስብሰባ ይደረግ ብለው ትእዛዝ ቢሰጡም የወያኔ ምክር ቤት አባላት የሆኑትና በሆነው መቀየማቸውን ፊት ለፊት ገልጸው የነበሩት ካድሬዎች ያለ አንዳች ፍርሃት አንሰበሰብም በሚል የጸና አቁዋም በመያዛቸው ስብሰባውን ማካሄድ ሳይቻል ቀርቶዋል ያለው ዘገባ በምክር ቤቱ አባሎች ድርጊት የተደናገጡት እነመለስ ዜናዊ የደህንነት ሃይሎችን አሰማርተው ክትትል እንዲደረግባቸው ባዘዙት መሰረት ተፈጻሚ መሆኑን አስረድቶዋል

በደህንነት ሃይሎች ስውር ክትትል እየተደረገባቸው የሚገኙት የወያኔ ምክር ቤት አባላት የሆኑት የብአዴን ሰዎች ይህ ዘገባ እስተገኘበት ግዜ ድረስ ሃሳባቸውን አለመቀየራቸውንም ለማወቅ ተችሎዋል

አንዱን የውስጥ ችግር ሳይፈቱት ሌላ የችግር አረንቁዋ ውስጥ መዘፈቅ እድል የሆነበት የወያኔ ቡድን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለፕሬዝደንቱ እና ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፍተኛ ሹማምንት ሙሉ ጥቅማ ጥቅም የሚያሰጥና እና ለሚኒስትሮች እና ለምክትል ሚኒስትሮችም የተሻለ ጥቅም እንዲሰጥ የሚያስችል ህግ አዘጋጅቶ ለራሳቸው ምቾት ተጨንቀው ቅድመ ዝግጅት ሲያደርጉ የተቀረውን የምክር ቤት አባላት የሹመት ግዜያቸው አብቅቶ ሲበተኑ የ3 ወር ደሞዝ ይከፈላቸው ብሎ ማለት እና ይህም እንደጥቅማጥቅም ይቆጠራል መባሉ ሌላ ጉሽምያ እንዲፈጠር አስችሎዋል

በዚህ የተነሳ ከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ ያሉት የወያኔ የምከር ቤት አባላት እርስ በእርስ የጎሪጥ እየተያዩ ከመሆኑም በላይ በተለይ ሌሎች የወያኔ የምክር ቤት አባላት ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርባቸው እና ክፍፍል እንዲፈጠር ለማድረግ ከወዲሁ ከፖለቲካ ጋር አያይዘው የተንኮል ቅስቀሳ እያደረጉባቸው መሆኑን ዘገባው አጋልጦዋል

ግንቦት ሰባት ከተባለው ድርጅት ጋር በተያያዘ ውስጣዊ ግኑኝነት ማድረጋቸው ተደርሶበታል ለዚህም ነው ይህንን ረቂቅ ህግ እና ሌሎችንም ሊቀበሉ የማይፈልጉት የሚለውን ባዶ የውንጀላ ታርጋ አዘጋጅተው « መስዋእትነት ከፍለው ለዚህ ያበቁንን ሰማእታቶች ንቀው ውስጥ ውስጡን ከፍተኛ ቅስቀሳ ጀምረዋል » በሚል ሽፋን ጀቡነው እነ በረከት ስምኦን በብአዴን የምክር ቤት አባሎች ላይ ጥብቅ ክትትል እንዲደረግ በማዘዛቸው በየሄዱበት ወከባው ተስፋፍቶ መቀጠሉን ዘገባው አብራርቶዋል

የህዝብና የቤቶች ቆጠራ ውጤት ለአንድ አመት ከስድስት ወር በላይ ሳይገለጽ በሚስጢር ተይዞ የነበረ ሲሆን በቅርቡ ይፋ ሲሆን ከፍተኛ ድንጋጤን መፍጠሩ ቀደም ሲል መዘገቡ አይዘነጋም የአማራ ክልልና የአዲስ አበባው ህዝብ ቁጥር መጭበርበሩን በማረጋገጥ በተለይ የወያኔው ዋነኛ ክንፍ የሆነው የብአዴን አባላት ጥያቄያቸው ውድቅ በመሆኑና በቅርቡም የጥቅማጥቅም ጉዳይ ላይ ስምምነት ላይ ሳይደርሱ መቅረታቸው በእነመለስ ዜናዊ ጥርስ የተነከሰባቸው መሆኑን በመረዳታቸው ተቃውሞዋቸውን አጠናክረው እያሰሙ ከመሆኑም በላይ ይህ ውሳኔ ፓለቲካዊ ነው ሲሉ በይፋ መናገር መጀመራቸው ታውቆዋል

የፖለቲካ ውሳኔ በአማራ ህዝብ ላይ ተሰጥቶዋል እያሉ ተቃውሞ እያሰሙ ያሉት የብአዴን ካድሬዎች ከወያኔ የተለያዩ ምስጢራዊ ጥቃቶች እየተሰነዘረባቸው መሆኑን በይፋና በአደባባይ መግለጽ በመጀመራቸው የወያኔን እኩይ ገመና አጋልጦዋል

እንዲህ አይነቱ ሴራ « አባል » በተባሉት የራስ ሰዎች ላይ መድረሱና መጋለጡ የግፈኛውን የወያኔ ቡድን የሴራ ተግባር አደባባይ ያወጣ ሆኖ በመገኘቱ በሽምግልና ለመያዝ እና እልባት ላይ ለመድረስ ግፈኛው ቡድን ጉንፋን ሲይዘው ሳል የሚጀምራቸው ህሊና ቢስ አባላቱ ተሰባብሶ እንዲቀርላቸው መፍጨርጨር ጀምረዋል

ያለ አንዳች ስራ እንደ እቃ ተጎልተው የሚውሉትና የአማራን ህዝብ በስሙ እየነገዱ የሚያተርፉበት ፤ ለጠባቡ የወያኔ ቡድን አባላት አሳልፈው የሰጡት እነአዲሱ ለገሰ እና ካድሬዎቻቸው አሁን እየፈጸሙ ላሉት በአባላቶቻቸውና በጦር አለቆች ላይ የሚደርሰውን ግፍ እያዩ እንዳላየ ሆነው መቀመጣቸው ይበልጥ የሚያበሳጭ ነው የሚሉት አመሻሹ ላይ ሆድ የባሳቸው ካድሬዎችና አባላት እያወገዙዋቸው መሆኑንም ለማወቅ ተችሎዋል

መለስ ዜናዊ እና በረከት ስምኦን ባለባቸው ስጋት የተነሳ በተለይ በብአዴን ላይ የጀመሩትን የምንጠራ ዘመቻ ከየጦሩ ክፍል እና የሲቪል ተቁዋማቱ ያለምንም ምክንያት አፍሰው እያሰሩዋቸው ከመሆኑም በላይ አንዳንዶቹን የት እንዳሰሩዋቸው እንኩዋን ሳይታወቅ ቤተሰቦቻቸው በፍለጋ እየተንከራተቱ መሆኑን የገለጸው ዘገባ በዚህ ሁሉ ጥቃት የህሊና ቢሱ አዲሱ ለገሰ እና ተከታዮቹ እጅ እንዳለበት ሊታወቅ ይገባል ያሉትን ግፉአን ጠቅሶ አስረድቶዋል

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በውስጣቸው መመሰቃቀል እጅግ ስላስቸገረው ስልጣን ለመልቀቅ ዝግጁ መሆኑን ሰሞኑን መናገሩ አመሉን ለሚያውቀው « ማስፈራራት ጀመረ » ከሚል የቡዋልት መልስ ያተረፈው ነገር አለመኖሩ ታውቆዋል

ሰሞኑን የወያኔው መሪ በውስጣቸው ያለው መመሰቃቀል እጅግ ስላስቸገረው ስልጣን ለመልቀቅ ዝግጁ መሆኑን በተናገረበት ወቅት « እድሜ ልኬን ለተዋጋሁበት ድርጅት እንድለቅ የሚያስገሰድደን የጋራ ስምምነት ላይ እንደርሳለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ » በማለት ጠቅሶ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ስልጣንና የፓርቲውን ሊቀመንበርነት ለመልቀቅና በሙሉ በረሃ ባልቀመሱ ሰዎች መተካት እንደሚኖርበት እየተከራከረ መሆኑን ከንግግሩ ለመረዳት ተችሎዋል ከበረሃ የመጡ አዛውንቶች ጭምር ከስልጣናቸው ወርደው በአዳዲስ ካድሬዎች መተካት እንዳለበት የገለጸው መለስ ዜናዊ ቡድኑ አልለቅም ቢል እንኩዋን በራሱ ግዜ ከስልጣንና ከፓርቲው እንደሚለቅ መወሰኑን ገልጦዋል

ይሁን እንጂ በህዝብም በሃገርም ላይ ለ18 ዓመታት ስውርና ግልጽ ግፍ ሲፈጽም የቆየው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የራሴ ናቸው የሚላቸውን አዳዲስ ካድሬዎች ተክቶ እና በውስጣቸው እርስ በእርስ እንደ አዲስ አድርጎ ካዋቀረ በሁዋላ ስልጣን ሊለቅ ማሰቡ እራሱንም ሎሌዎቹንም ለማዳን ሲል የሚደርገው መሆኑን አስተያየት ሰጪዎች ይስማሙበታል

ስልጣን እለቃለሁ እያለ ሲወተውት የነበረው መለስ ዜናዊ መልሶ እስክሞት ድረስ ፓርቲዬን አልለቅም ብሎዋል አንድ ግዜ ስልጣን በቃኝ ሌላ ግዜ ፓርቲዬ አስገደደኝ፤ ደግሞ ሌላ ቀን ፓርቲዬንም ቢሆን እለቃለሁ ሌላ ግዜ ደግሞ አልለቅም ፤ አልተውም ፤ የሚለውና የሚዘባርቀው መለስ ዜናዊ በአባላቱ መካከል ከግዜ ወዲህ እየተጠናከረ በመጣው የልዩነት መስፋት የሚናገረውንና የሚያደርገውን እስከሚያጣበት ደረጃ አድርሶታል ሲሉ ለወያኔ ደርጅት ቅርበት ያላቸው ምንጮች መናገራቸውን ዘገባው አስረድቶዋል

በዚህ ወቅት በወያኔ ቡድን አባላት ይህ ጥያቄ ቀርቦ በውይይት ላይ የሚገኝ ሲሆን በመጪው መስከረም ወር መጀመሪያ ላይ በሚደረገው የወያኔ ጠቅላላ ጉባኤ በሚካሄድበት ወቅት ውሳኔ ይሰጠዋል ተብሎ ሲገመት አሁን የተከሰተው ውስጣዊ ፍትጊያም በድርጅታዊ ጉባኤው ወቅት እልባት ያገኛል ተብሎዋል

በተለይ የወያኔው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን የመለስ ዜናዊን ቦታ ይተካ የሚለው የጥቂት የዋኻን ግምት እና አስተያየት ውዝግብ አስነስቶ እንደነበርም ከወያኔ አባላት አፈትልኮ የወጣው መረጃ ይጠቁማል

በዚህ ጥቆማ ላይ ተቃውሞውን ያቀረበው አንዱ አርከበ እቁባይ ሲሆን እርሱም የውጪ ፖሊሲውን እና ዲፕሎማሲውን ያጉዋደለ ሰው ለዚህ ቦታ እንዴት ብቁ ሊሆን ይችላል በማለት ተቃውሞታል

በረከት ስምኦንና መለስ ዜናዊ በበኩላቸው ልምድ ያለው ከእርሱ የተሻለ ሰው ለግዜው የለም ለግዜው ለአንድ ምርጫ ቦታውን ይያዘውና ይምራ በማለት የማስመሰያ ድራማቸው ሚዛን ደፊ እንዲሆን ሲጣጣሩ ተስተውሎዋል

የአፍ እላፊ እስከሚሰነዝር ደረጃ አድርሶዋቸው በነበረው በዚሁ ውይይት ላይ አርከበ እቁባይና እነበረከት ሳይግባቡ በመዘላለፍ እና በመነቃቀፍ ግዜ ማጥፋታቸውም በወያኔ ውስጥ ስር እየሰደደ ለመጣው ችግር ማሳያ መሆኑን የሚናገሩ አልታጡም

የተጀመረውና ማብቂያው የት እንደሚሆን ለመገመት የሚያዳግተው የወያኔ ቁርቁዋሶና የእርስ በእርስ አለመግባባት በመስከረም ወር በሚደረገው የወያኔ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ ጎልቶ ይወጣል ተብሎ ይገመታል

ስልጣን እለቃለሁ የሚለው መለስ ዜናዊ ቦታውን ማን እንደሚተካው ሳይሆን የሚያሳስበው በእርግጥ ስልጣን ለመልቀቅ ሳይሆን የተለመደ የማዘናጊያ ስልቱን ለመጠቀም ሲል የተናገረው መሆኑ ታውቆ የእርሱንና የቡድኑን ከስልጣን መነሳት ወይም ማስወገድ የሚቻለው በህዝብ የተባበረና የተጠናከረ ክንድ እንዲሁም በተቃውሞ ሃይላት ሁለገብ ትግል መሆኑን በመገንዘብ ለትግሉ መጠናከር ተገቢውን ሁሉ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ አንዳንድ ምሁራን መናገራቸው በዘገባው ተመልክቶዋል

ዛሬ ስልጣን እለቃለሁ የሚለው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከ400 በላይ ዜጎችን በግፍ አስገድሎ በአንድ ጉድጉዋድ ውስጥ እንዲቀበሩ ያስደረገ ፤ የአኝዋኩ ፤ የወተሩ ፤ የበደኖው ፤ የአርባጉጉው ፤ በሌላውም የግፍ ተግባሩን በንጹሃን ዜጎች ላይ እንዲደርስ ካደረገ በሁዋላ እንኩዋን በ1997 ዓ.ም. በመቶዎች በሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ግድያ እንዲፈጸም ትእዛዝ የሰጠ ፤ የመራ ፤ ያስተባበረ ፤ በሺህዎች የሚቆጠሩ እንዲታሰሩ ፤ እንዲሰደዱ ያደረገ ፤ የአውሬ ምግባር ያለው ሰው ራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን ሲል ስልጣን እለቃለሁ ቢል በግፍ የፈሰሰ የንጹሃን ደም ሊፋረደው እንደሚችል እና መቼም ሆነ መቼም ከህግ እንደማያመልጥ ሊታወቅ እንደሚገባ በብዙዎች ዘንድ ይታመናል

ፓርቲዬ የማይለቀኝ ከሆነ እንኩዋን በራሴ ግዜ ከፓርቲውም እለቃለሁ እያሉ መደንፋት እና ጉራ መቸርቸርን ስራዬ ብሎ የያዘው መለስ ዜናዊ የተፋውን ምራቅ

ለመላስ በሞኖፖል በተቆጣጠረው ቴሌቭዥን በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ደግሞ ስድስት ክንድ መሬት እስከምንተራስ ድረስ ፓርቲዬን አልለቅም በማለት ሲናገር ተደምጦዋል

በስልጣን ላይ በቆየበት አመት ሁሉ ብቅ እያሉ ስልጣን ልለቅ ነው ማለትና ቤተ መንግስቱን በሶስት ዙር የተጠናከረ ቅልብ ወታደር እንዲጠበቅ ማድረግ ማንን ለማዘናጋት ሲባል እንደሚባል አይገባንም የሚሉ አስተታየት ሰጪዎች መኖራቸውንም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል

በሌላ በኩል በአገሪቱ ውስጥ በተከሰተው የረሃብ አደጋ ህይወታቸው አጠያያቂ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ወገኖች የእርዳታ እህል እንዳያገኙ ለጋሾች እርዳታቸውን ወደ አገር ውስጥ እንዳያስገቡ መከልከላቸው ታወቀ

ከ10 ሚሊዮን በላይ ህዝብ በከፋ የረሃብ አደጋ ተጋርጦበት እያለ የአለም የምግብ ፕሮግራም የእርዳታ እህል በጂቡቲ በኩል እንዲደርስና በአስቸኩዋይ ለተራቡ ወገኖች እንዲደርስ ቢልም የወያኔ ቡድን ግን ለረሃብተኛው የሚሆን እህል ሳይሆን ማዳበሪያ እንዲጉዋጉዋዝ ቅድሚያ በመስጠቱ የደረቅ ጭነት ተሽከርካሪዎች እህሉን ትተው ማዳበሪያውን እየጫኑ እንደሚገኙ ከዘገባው ለመረዳት ተችሎዋል

እነዚህ መኪኖች የእርዳታውን እህል እንዳይጭኑ መመሪያ ተሰጥቶዋቸው ከጂቡቲ ወደብ የማዳበሪያ ጭነት እየጫኑ እንዲያጉዋጉዙ መደረጉንና ይህን በማያደርጉ የጭነት መኪኖች ባለንብረቶች ላይ እርምጃ በመውሰድ ለእስራትም እንደሚበቁ የጠበቀ መስፈራሪያ የተሰጣቸው መሆኑም ታውቆዋል

ህዝብ በረሃብ አለንጋ እየተገረፈ ባለበት ወቅት ከምስኪኑ ገበሬ ላይ ትርፍ ለማጋበስ ሲባል የማዳበሪያ ሽያጭ ላይ ማተኮሩ የወያኔዎችን ገንዘብ ከሰው ህይወት እንደሚበልጥበት ያረጋገጠ አጋጣሚ ነው ሲሉ ተቺዎች መናገራቸው ተዘግቦዋል

ህዝብ በረሃብ እየተቆላ እና እያለቀ ባለበት በአሁኑ ወቅት በርካሽ ዋጋ እየገዙ በገበሬው ላይ በውድ ዋጋ የሚሸጡት ማዳበሪያ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የሚያደርጉት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት የራሳቸውን ስህተት ወደሌላው እንዲላከክ በመፈለጋቸው ያለምንም ይሉኝታና ሃፍረት ሲለጥፉ መደመጣቸው አሳፋሪ መሆኑን የገለጸው ዘገባ በረሃብተኞቹ ስም የመጣው የእርዳታ ስንዴ በአሁኑ ወቅት ወደብ ላይ እየበሰበሰ መሆኑን የአለም ምግብ ፕሮግራም ምንጮች አጋልጠዋል

ወያኔ ግን የለጋሽ ወገኖች የፈጠሩት ችግር ነው በማለት መናገሩ ትዝብት ላይ ጥሎታል ቅድሚያ የዜጎችን ህይወት መታደግ የሚገባ መሆኑ አያጠያይቅም የሚለው

ዘገባ ስግብግብ ባህሪያቸው ስለበለጠባቸው ከረሃብተኛው ህይወት የግል ንግዳቸው በልጦባቸው በሚሊዮኖች ህይወት ላይ ሲያላግጡ መስተዋሉ አሳዛኝ አድርጎታል

በሌላ ተመሳሳይ ዜና ህዝብ በረሃብ እየተገረፈና አገሪቱ ወያኔ አመጣሽ በሆነ የኢኮኖሚ ድቀት ውስጥ ተዘፍቃ በምትገኝበት በአሁኑ ወቅት የወያኔ ባለስልጣናት ህዝብንና አገርን ወደመቀመቅ እየከተቱት ለራሳቸው በአብዛኛው እያሰባሰቡ ከመሆኑም የገለጸው ዘገባ በተለይ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን እየሰራች ያለችው ስራ እጅግ አስገራሚ እና አሳዛኝ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገለጠ

በሃገር ውስጥ የዶላር እጥረት በማጋጠሙ የንግዱ ማህበረሰብ እንቅስቃሴ እግር ከወርች ታስሮ ባለበት ወቅት እንደፈለገች በመረጠችውና ያዋጣኛል ባለችው የንግድ ስራ ላይ ያለምንም ፈቃድ እየገባች እንደምትንቦራጨቅበት የገለጸው ዘገባ በጥቁር ገበያ ንግድ ተሰማርታ ከፍተኛ ገንዘብ እያሸሸች መሆኑን አስረድቶዋል

አገር በረሃብ ያልቃል በኢኮኖሚ ድቀት ሽባ ይሆናል ፤ ወያኔዎች ግን ከህዝብ ጉሮሮ እየነጠቁ አንጠሱራ ሃብት ማሸሽ መጀመራቸው በእርግጥም የዛሬ ድርጊታቸው ሳይሆን የቆየና የነበረ ነው ሲሉ መዘረፍና መነጠቅ ከጀመሩን መቆየታቸውን የሚያውቁ ይናገራሉ